# ሞት ! እንዳትቀድመኝ!

## 1.

ሞት እኔ አልፈራህም አንተ ለማን ቀርተህ!
ግን ብትሰማ አድምጠኝ አለ የምጠይቅህ!
መጣደፍ፤ መቸኮል ትወዳለህና፤
ተንሽ አደብ ሰጥቶህ ሕሊና ግዛና፤
ቢቻልህ  አትቸኩል፤ አትሩጥ ፤አትገስግስ፤
የልቤ እስኪሞላ ትንሽ ጊዜ ታገስ።

ጊዜ ያበቀለው እሾህ፤ አሜኬላ፤
የሕዝብ፤ የሐገር ጠንቅ፤ እንክርዳድ አተላ፤
የዘመኑን  ኒሮ፤ ፋሽስት አረመኔ፤
አገርን የሚሸጥ ከፋፋይ  ወያኔ፤
ከተቀመጠበት ሲውርድ ተሽቀንጥሮ፤
በሕግ ተገዶ ከስልጣን ተባሮ፤
ከፍርድ ቤት ቀርቦ፡ “በል አስረዳ!” ሲባል፤
ግፉን በጠቅላላ የዋለውን በደል፤
ወንድ፤ሴት አላለ ወይ  ወጣት ጎልማሳ፤
ለባልቴት፤ ለአዛዉንት ለማንም ሳይሳሳ፤
በጨካኙ ክንዱ በግፍ ላጨዳቸው፤
ደማቸው ደመ ከልብ እንዳይሆንባቸው፤
ዕዉነት መስክራበት  ሲፈረድበት፤
“ዕድሜ ይፍታህ!” ወይ ሞት ሲበየንበት፤
እጅ እግሩን የፍጢኝ ታስሮ በገመድ፤
በተራው ሊማቅቅ ከርቸሌ ሲወርድ፤
ይህን ባይኔ ዓይቼ ልሙት በማግስቱ፤
እስከዚያ አደራህን እንዳትቸኩል ሞቱ።

## 2.

ትራፊ ለቃሚን፤ አድርባይ ሆዳሙን፤
ሁሉን ቀባጣሪ፤ ለፍላፊ አዝማሪውን፤
ሰላይ፤ ፊርማቶሪ፤  ሥርጎ  ገብ ተኩላውን፤
አርባ  ሳዝልጠው ባኮርባቹ ጀርባውን
በሽመል፤ በዱላ ሳላገላብጠው፤
ምጥ እንዳያዛት ሴት ሳላንቆራጥጠው፤
ጊዜ ባለ ዉሉ ይህን ዕድል ስጠኝ፤
ግዳጄን ልፈጽም መብቴን አትንፈገኝ።
እንደተቆጣ ንብ ተነቃንቆ  ቀፎው፤
ጊንጥ እባቡን  ሆኜ  ጠላቴን  ስነድፈው፤
በጥይት  ሳልፈልጠው፤ ግንባሩን በመውዜር፤
እንብርቱን  በሳንጃ፤ ሆዱን  ሳልተረትር፤
ኩላሊቱን  ሳልጠብስ፤ ሳንባውን ሳልመትር፤
የከሰለው ሆዴ፤ አንጀቴ  ሳይርስ፤
ያሰብኩት ሳይሞላ፤ የልቤ ሳይደርስ፤
ሞት  እንዳትቸኩል   እዳታጣድፈኝ፤
ብዙ አልጠይቅህም ትንሽ ጊዜ  ስጠኝ።
አሰብ ከሄደበት በግድ ተመልሶ፤
የጠፋው ስማችን ፤ ክብራችን ታድሶ፤
ኢትዮጵያን ሳናደርግ  የወደብ ባለቤት፤
ይህን ባይኔ ሳላይ እዳትቀድመኝ  ሞት።
አባይ ተገድቦ ኢትዮጵያን  ሲያለማ፤
አርሲና፤ ሐረርጌ፤ ባሌና፤ ሲዳማ፤
ጎጃም፤አዳ፤ ብቾ፤ ቡልጋና፤ ሁመራ፤
በደንብ ለምቶ አይቼው ሲተርፈን አዝመራ፤
እኛም በተራችን ለቸገረው ስንቸር፤
ኢትዮጵያ  ለካንሳስ  ስንዴ ስታበድር፤

## 3.

የአፍሪካ ማፈሪያ መናጢ ድሃዎች፤
መባላችን ቀርቶ ሁል ጊዜ ለማኞች፤
መሰደድን ንቀን ስኖር ባገራችን፤
ሌሎች ስናስጠጋ  እኛም  በተራችን፤
ይህን ቀን ዓይቼ ልሙት በማግስቱ፤
ግድየለም ታገሰኝ አትቸኩል ሞቱ
አገር ሰላም ሆና አቧራው ሲረጋ፤
ሕዝብን የሚያገናኝ መንገድ ሳንዘረጋ
ሁስፒታል ተሰርቶ ክሊንክ ተስፋፍቶ’
ኮሌጅ፤ ዩኒቨርሲቲ  በየትም  ተሰርቶ፤
ይህን ሁሉ ዓይቼ ደስ ሳይለኝ!
አደራ እንዳትቸኩል ሞት እንዳትቀድመኝ!!

## 4.

ላንድነት፤ ለሰላም፤ ለሕብረት፤፡ለፍቅር፤
አንደበተ  ጨዋ  ተከብሮ  የሚያስከብር፤
“ሐገሬ! ወገኔ!”  የሚል  መሪ  ሲገኝ፤
ከዚያ እንደፈለገህ  እንዳሻህ  አድርገኝ።

ይፍሩ ኃይሉ
ነሓሴ 2002

www.ethiomedia.com – a site of alternative news and views
August 31, 2010